# ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ፦

**ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአርባ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አርባ ሦስት ጊዜ ስሟ ተጠቅሶ ይገኛል። እዚህ ላይ ልብ ልንልና ልናስተውለው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ስሟያልተጠቀሰበት - ሆኖም ግን ስለ ኢትዮጵያ የተነገረ ታሪክ ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መኖሩ ሊዘነጋ እንደማይገባው ነው።**

**ኢትዮጵያ ፤ በሳባ ,የሳባ ምድር. እየተባለች ትታወቃለች ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነን በታሪክ ከተገለጹት ማስረጃዎች ባሻገር በመጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ ነገሥት ፲፡፩-፲፫ እና በመጽሐፈ ዜና ካልዕ ፱፡፩-፲፪ ላይ ተገልጾ እንደሚገኘው ቃል የሳባ (የኢትዮጵያ) ንግሥት ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠውን እውቀትና ጥበብ ለማድነቅ እጅ መንሻ ይዛ እንደሄደች እና ለዚህ ክብር ያበቃው እግዚአብሔር መሆኑን የገለጸችበት ታሪክ ፤ በሌላ መልኩም ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ስጦታ እንደሰጣትና የጠየቀችውንም ሁሉ እንዳደረገላት የሚገልጽ ጽሑፍ ተጽፎ ይገኛል። ለዚህም የታቦተ ፅዮን በኢትዮጵያ መገኘት ፤ የኦሪት መሥዋዕት የሚሰዋባቸው ስፍራዎች በኢትዮጵያ መኖር የሳባ ንግሥት ኢትዮጵያዊት ለመሆንዋ ሌላው ማስረጃ ነው።**

**በመጽሐፈ ነገሥት ፲፡፩-፲፫ እና በመጽሐፈ ዜና ካልዕ ፱፡፩-፲፪ ላይ ሙሉ ታሪኩ የተጻፈበትን ይህንን ክፍል በማንበብ ሌሎች መጻሕፍት ይህንን ሀሳብ መነሻ አድርገው ስለ ኢትዮጵያ የጻፉትን ማገናዘብ ያስፈልጋል።**

## መግለጫ፦

**ይህ መልእክት የተገኘበት የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የታተመው ሲሆን የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ (BIBLE) ደግሞ ከሁለት ዓይነት መጽሐፍ ላይ ስያሜውም KING JAMES REFERENCE እና HOLY BIBLE with the APOCRYPHAL/DEUTEROCANONICAL BOOKS ከሚለው የተገኘ ነው። መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ፣ መጽሐፈ ዮዲት እና ተጨማሪው መጽሐፈ አስቴር (ESDRAS, JUDITH and ADDITION TO ESTHER) በእንግሊዝኛው APOCRYPHAL/DEUTEROCANONICAL BOOKS ከተሰኘው HOLY BIBLE ላይ ነው።**

**በመጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ፣ በመጽሐፈ ዮዲት እና በተጨማሪው መጽሐፈ አስቴር ላይ ስለ ኢትዮጵያ ተጽፈው የሚገኙት ቦታዎች በሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ስድሳ ስድስቱ ተብሎ በሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። (መጽሐፈ አስቴር ፮፡፱ን) አይመለከትም። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ (2ኛ ዕዝራ) ላይ ተጽፎ የሚገኘው የኢትዮጵያ ስም ያለበት ጥቅስ በእንግሊዝኛው ACROPHYPICAL/DEUTRO CANONICAL BOOKS/ ተብሎ በሚታወቀው መጽሐፍ ላይ 1 ESDRAS (1ኛ ዕዝራ) ሆኖ ይገኛል ፤ ምእራፍና ቁጥሩ ግን አንድ ነው።**

**በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ስድሳ ስድስቱ ተብሎ በሚታወቀውም ሆነ በሰማንያ አሐዱ ላይ መጽሐፈ አስቴር ተብሎ የተሰየመ ክፍል አለ ፤ ስለ ኢትዮጵያ የተጻፈበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚገኘው አስቴር ፮፡፱ በስድሳ ስድስቱ እንዲሁም አስቴር ፮፡፩ በሰማንያ አሐዱ ላይ ነው። በእንግሊዝኛው APOCRYPHAL/DEUTEROCANONICAL BOOKS/ተብሎ በሚታወቀው መጽሐፍ ላይ ሁለቱ የአስቴር መጻሕፍት መለያቸው መጽሐፈ አስቴር/BOOKS OF ESTHER_እና ተጨማሪ አስቴር/ADDITIONAL ESTHER በሚለው ቃል ነው። አስቴር ፮፡፩ በአማርኛው - አስቴር ፲፫፡፩ በእንግሊዝኛው ላይ ይሆናል።**

**ከዚህ በታች በአርባ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አርባ ሦስት ጊዜ ስሟ ተጠቅሶ የሚገኘው ኢትዮጵያ ከተጠቀሰችበት ክፍል ላይ ያለውን ሙሉ መልእክት ይመልከቱ። የእንዳንዶቹን ጥቅሶች ሙሉ መልእክት ለመረዳት ጥቅሱ ከተጻፈበት ፊትና ኋላ ያሉትን መልእክቶች በደንብ ማንበብ ያስፈልጋል።**

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ጥቅሶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ፦

፩- የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው ፤ እርሱም **የኢትዮጵያን** ምድር ሁሉ ይከብባል
ኦሪት ዘፍጥረት (ዘፍ.፪፡፲፫)

፪ - ሙሴም **ኢትዮጵያይቱን** አግብቶአልና ባገባት **በኢትዮጵያይቱ** ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ። ኦሪት ዘኁልቁ (ዘኁ. ፲፪፡፩)

፫ - እርሱም። **የኢትዮጵያ** ንጉሥ ቴርሐቅ ሊወጋህ መጥቶአል የሚል ወሬ በሰማ ጊዜ ደግሞ ወደ ሕዝቅያስ መልእክተኞችን ላከ ፥ እንዲህ ሲል።
መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ (፪ኛ.ነገ ፲፱፡፱)

፬ - ከእርሱም ጋር ከግብጽ ለመጣው ሕዝብ ቍጥር አልነበረውም ፤ እነርሱም የልብያ ሰዎች ፥ ሱካውያን ፥ **የኢትዮጵያ** ሰዎችም ነበሩ።
መጽሐፈ ቀዳማዊ ካልዕ (፪ኛ.ዜና ፲፪፡፫)

፭- **ኢትዮጵያዊውም** ዝሪ አንድ ሚሊዮን ሰዎችና ሦስት መቶ ሰረገሎች ይዞ ወጣባቸው ፤ ወደ መሪሳም መጣ። መጽሐፈ ቀዳማዊ ካልዕ (፪ኛ.ዜና ፲፬፡፱)

፮- እግዚአብሔርም በአሳና በይሁዳ ፊት **ኢትዮጵያውያንን** መታ **ኢትዮጵያውያንም** ሸሹ።
መጽሐፈ ቀዳማዊ ካልዕ (፪ኛ.ዜና ፲፬፡፲፪)

፯- አሳም ከእሱም ጋር ያለው ሕዝብ እስከ ጌራራ ድረስ አሳደዱአቸው **ኢትዮጵያውያንም** ፈጽመው እስኪጠፉ ድረስ ወደቁ ፥ በእግዚአብሔርና በሠራዊቱ ፊት ተሰባብረዋልና ፤ እጅግም ብዙ ምርኮ ወሰዱ። መጽሐፈ ቀዳማዊ ካልዕ (፪ኛ.ዜና ፲፬፡፲፫)

፰- **ኢትዮጵያውያንና** የልብያ ሰዎች እጅግ ብዙ ሰረገሎችና ፈረሰኞች የነበሩአቸው እጅግ ታላቅ ጭፍራ አልነበሩምን? በእግዚአብሔር ስለ ታመንህ በእጅህ አሳልፎ ሰጣቸው ፥
መጽሐፈ ቀዳማዊ ካልዕ (፪ኛ.ዜና ፲፮፡፰)

፱- እግዚአብሔርን በፍልስጥኤማውያንና **በኢትዮጵያውያን** አጠገብ የሚኖሩትን የዓረባውያንን መንፈስ በኢዮራም ላይ አስነሣ። መጽሐፈ ቀዳማዊ ካልዕ (፪ኛ.ዜና ፳፩፡፲፮)

፲ -በአርጤክስስም ዘመን እንዲህ ሆነ ፤ ይህም አርጤክስስ ከህንድ ጀምሮ እስከ **ኢትዮጵያ** ድረስ በመቶ ሀያ ሰባት አገሮች ላይ ነገሠ። መጽሐፈ አስቴር (አስቴ. ፩-፩)

፲፩- በዚያን ጊዜም ኒሳን በተባለው በመጀመሪያው ወር ከወሩም በሀያ ሦስተኛው ቀን የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠሩ ፤ መርዶክዮስም ስለ አይሁድ እንዳዘዘው ሁሉ ከህንድ ጀምሮ እስከ **ኢትዮጵያ** ድረስ በመቶ ሀያ ሰባቱ አገሮች ላሉ ሹማምትና አለቆች አዛውንት ለእያንዳንዱም አገር እንደ ጽሕፈቱ ለእያንዳንዱም ሕዝብ እንደ ቋንቋው ለአይሁድም እንደ ጽሕፈታቸውና እንደ ቋንቋቸው ተጻፈ። መጽሐፈ አስቴር (አስቴ ፰፡፱)

፲፪- **የኢትዮጵያ** ቶጳዝዮን አይተካከላትም ፥ መጽሐፈ ኢዮብ (ኢዮ.፳፰፡፲፱)

፲፫- መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ ፤ **ኢትዮጵያ** እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።
መዝሙረ ዳዊት (መዝ. ፷፰፡፴፩)

፲፬- የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ ፤ እነሆ ፥ ፍልስጥኤማውያን ጢሮስም **የኢትዮጵያም** ሕዝብ ፥ እነዚህ በዚያ ተወለዱ። መዝሙረ ዳዊት (መዝ. ፹፯፡፬)

፲፭- **በኢትዮጵያ** ወንዞች ማዶ ላለች ፥ ክንፍ ያላቸው መርከቦች ላሉባት ፥
መጽሐፈ ኢሳይያስ (ኢሳ.፲፰፡፩)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

፲፯- እግዚአብሔርም አለ። ባሪያዬ ኢሳይያስ በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ ሦስት ዓመት ለምልክትና ለተአምራት ሊሆን ራቁቱንና ባዶ እግሩን እንደ ሄደ ፥
ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ.፳፥፫)

፲፰- እንዲሁ የአሦር ንጉሥ የግብጽንና የኢትዮጵያን ምርኮ ፥ ጕበዛዝቱንና ሽማግሌዎቹን ፥ ራቁታቸውንና ባዶ እግራቸውን አድርጎ ገላቸውንም ገልጦ ፥ ለግብጽ ጕስቍልና ይነዳቸዋል። ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ.፳፥፬)

፲፱- እነርሱም ከተሰፋቸው ከኢትዮጵያ ከትምክሕታቸውም ከግብጽ የተነሣ ይፈራሉ ያፍራማል ፤ ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ.፳፥፭)

፳- አርሱም። የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሊዋጋህ መጥቶአል የሚል ወሬ ሰማ። በሰማም ጊዜ ወደ ሕዝቅያስ መልእክተኞችን ላከ ፥ ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ.፴፯፥፱)

፳፩- እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ ፤ ግብጽን ለአንተ ቤዛ አድርጌ ፥ ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ፋንታ ሰጥቻለሁ።
ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ.፵፫፥፫)

፳፭- እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። የግብጽ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረጅሞችም የሳባ ሰዎች ወደ አንተ ያልፋሉ ፤ ለአንተም ይሆናሉ እጆቻቸውም ታስረው ይከተሉሃል ፤ በፊትህም ያልፋሉ ፥ ለአንተም እየሰገዱ። በእውነት እግዚአብሔር በአንተ አለ ፥ ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም ብለው ይለምኑሃል። ትንቢተ ኢሳይያስ (ኢሳ.፵፭፥፲፬)

፳፪- በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ።
ትንቢተ ኤርምያስ (ኤር. ፲፫፥፳፫)

፳፫- በንጉሡም ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርምያስን በጕድጓዱ ውስጥ እንዳኖሩት ሰማ። ንጉሡም በብንያም በር ተቀምጦ ነበር።
ትንቢተ ኤርምያስ (ኤር. ፴፰፥፯)

፳፬- ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክም። ከአንተ ጋር ሠላሳ ሰዎች ከዚህ ውሰድ ፥ ነቢዩም ኤርምያስ ሳይሞት ከጕድጓድ አውጣው ብሎ አዘዘው።
ትንቢተ ኤርምያስ (ኤር. ፴፰፥፲)

፳፭- ኢትዮጵያዊውም አቤሜሌክ ኤርምያስን። ይህን አሮጌ ጨርቅና እላቂውን ልብስ በብብትህ ከገመዱ በታች አድርግ አለው ፤ ኤርምያስም እንዲሁ አደረገ።
ትንቢተ ኤርምያስ (ኤር. ፴፰፥፲፪)

፳፮- ሂድ ለኢትዮጵያዊውም ለአቤሜሌክ እንዲህ በለው። የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። እነሆ ፥ ለበጎነት ሳይሆን ለክፋት ቃሌን በዚህች ከተማ ላይ አመጣለሁ ፤ በዚያም ቀን በፊትህ ይፈጸማል።
ትንቢተ ኤርምያስ (ኤር. ፴፱፥፲፮)

፳፯- ስለዚህ ፥ እነሆ ፥ በአንተና በወንዞችህ ላይ ነኝ ፥ የግብጽንም ምድር ከሚግዶል ጀምሮ እስከ ሴዌኔና እስከ ኢትዮጵያ ዳርቻ ድረስ ውድማና ባድማ አደርጋታለሁ።
ትንቢተ ሕዝቅኤል (ሕዝ. ፳፱፥፲)

፳፰- ሰይፍ በግብጽ ላይ ይመጣል ፥ ሁከትም በኢትዮጵያ ይሆናል ፤ የተገደሉትም በግብጽ ውስጥ ይወድቃሉ ፥ ብዛትዋንም ይወስዳሉ ፥ መሠረትዋም ይፈርሳል።
ትንቢተ ሕዝቅኤል (ሕዝ. ፴፥፬)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

፳፱- ኢትዮጵያና ፋጥ ሉድም የተደባለቀም ሕዝብ ሁሉ ኩብም ቃል ኪዳንም የገባችው ምድር ልጆች ከእነርሱ ጋር በሰይፍ ይወድቃሉ።
ትንቢተ ሕዝቅኤል (ሕዝ. ፴፡፭)

፴- በዚያ ቀን መልእክተኞች ተዘልለው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን ለማስፈራት ከፊቴ በመርከብ ይወጣሉ ፤ እንደ ግብጽም ቀን ሁከት ይሆንባቸዋል ፤ እነሆ ፥ ይመጣልና።
ትንቢተ ሕዝቅኤል (ሕዝ. ፴፡፱)

፴፩- ፋርስንና ኢትዮጵያን ፋጥንም ከእነርሱ ጋር ጋሻና የራስ ቁርን የለበሱትን ሁሉ ፥
ትንቢተ ሕዝቅኤል (ሕዝ. ፴፰፡፭)

፴፪- በወርቅና በብርም መዝገብ ላይ ፥ በከበረችም በግብጽ ዕቃ ሁሉ ላይ ይሠለጥናል ፤ የልብያና የኢትዮጵያ ሰዎችም ይከተሉታል። ትንቢተ ዳንኤል (ዳን. ፲፩፡፵፫)

፴፫- የእስራኤል ልጆች ሆይ ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር። እስራኤልን ከግብጽ ምድር ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ከከፍቶር ፥ ሶርያውያንንም ከቂር አለወጣሁምን? ትንቢተ አሞጽ (አሞጽ ፱፡፯)

፴፬- ኢትዮጵያና ግብጽ የማይቁጠር ኃይልዋ ነበሩ ፤ ፋጥና ልብያ ረዳቶችዋ ነበሩ።
ትንቢተ ናሆም (ናሆም ፫፡፱)

፴፭- እናንተም ኢትዮጵያውያን ደግሞ ፥ በሰይፌ ትገደላላችሁ።
ትንቢተ ሶፎንያስ (ሶፎ. ፪፡፲፪)

፴፮- ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ ፥ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ፥ ቍርባኔን ያመጡልኛል። ትንቢተ ሶፎንያስ (ሶፎ. ፫፡፲)

፴፯- ዕራቅ ማሠሮችና ለደጃዝማቾች ሁሉ መቶ ሃያ ሰባት ምስፍና ላሉባት ለሕንደኬ ሰዎች ሁሉና ለሹማምንቱ ሁሉ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ላሉ ሰዎች ደግ በዓል አደረገ።
መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ፫፡፪ (፪ኛ. ዕዝራ ፫፡፪)

፴፰- ወደ ሚኒዎስም እስከ ኢትዮጵያ አውራጃ ድረስ በግብፅ ወደሚኖሩም ሰዎች ሁሉ ላከ።
መጽሐፈ ዮዲት (ዮዲት ፩፡፲)

፴፱- የገናናው ንጉሥ የአርጤክስስ እነዚያ መጻሕፍቶች ለኢትዮጵያና ለሀንድ አገር ለመቶ ሃያ ሰባቱም አገሮች ለመኳንንቱና ለሹማምንቱም ይድረሱ ፤ ተድላ ደስታን በማብዛት በመራራትም ለምትረቡአቸው፡ ለምትጠቅሙአቸው ለእናንተ በኛ መልክት።
መጽሐፈ አስቴር (አስቴር ፰፡፭)

፵- ተነሥቶም ሄደ። እነሆም ፥ ሀንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር ፤ ሐዋርያት ሥራ (ሐዋ. ፰፡፳፯)

ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ! !

_____//_____

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)